# ያለአግባብ ሃብት ያፈሩ የመንግስት አመራሮችን የመፈተሽ ስራ ተጀምሯል

ጥር 1 ፣ 2008 በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ያለአግባብ ሃብት ያካበቱ የመንግስት አመራሮችን የመፈተሽ ስራ መጀመሩን የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ተናገሩ።

"የመልካም አስተዳደር ችግሮች እስካሁን አለመፈታታቸው ድክመት ቢሆንም ችግሮቹን ከመፍታት አንጻር የመንግስት ቁርጠኝነት ላይ ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም" ብለዋል ሚንስትሩ።

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚንስትርና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪ ዶ/ር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ከኤፍቢሲ ጋር በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ቃለ-መጠይቅ አድርገዋል።

በዚህ ወቅት ሚኒስትሩ እንዳሉት መልካም አስተዳደርን ጨምሮ የቀጣይ አምስት ዓመታት የአገሪቱ እቅዶች በተወካዮች ምክር ቤት ጸድቀው እቅዶቹን በየደረጃው የማውረድ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

"እስካሁን በነበረው ሂደት የመልካም አስተዳደር ስራ ከልማት መለየት አልነበረበትም ይሔ ድክመት ነው፤ የመልካም አስተዳደር ጉድለቱ ከቀጠለ ልማቱም የማይኖር በመሆኑ መንግስት ከልማት ጋር በማስተሳሰር ችግሮቹን ለመፍታት ቁርጠኛ ነው" ብለዋል።




መልካም አስተዳዳር በሂደት የሚመጣ ቢሆንም ህዝቡን እያማረሩ የሚገኙ አካላትን ፈጥኖ የማረምና የማስተካከያ እርምጃዎች የመውሰድ ስራ እየተሰራ መሆኑንም ነው ሚኒስትሩ የገለጹት።

ከዚህ በሻገር በራሳቸውም ሆነ በቤተሰባቸው በኩል ከአቅም በላይ ንብረት ያላቸው አመራሮች ራሳቸውን ግልጽ የሚያደርጉበትና የሚፈተሹበት አሰራር መጀመሩን ጠቁመዋል።

በመልካም አስተዳደር ጉድለትና ሙስና ላይ የህብረተሰቡ ጥቆማ ወሳኝ ቢሆንም አሰራሩ ከህብረተሰቡ ጥቆማ በተጨማሪ መንግስት የራሱን የፍተሻና የእርምጃ ስራ እንደሚሰራ የሚያረጋግጥ ነው ማለታቸውን ኢዜአ ኤፍቢሲን ጠቅሶ ዘግቧል።